PANORAMA # 8

የትዝብት አድማስ

ታህሳሥ 29 2000 ዓም

# የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ልጆች፥ የየቤተሰቦቻቸውን ከብቶች ለግችጦሽ የሚያስማሯቸው በአንድ ላይ ሆነው ነው፡፡ ከብቶቹ ርቀው እንዳይሄዱም ሆነ የሰው አዝመራ እንዳያበለሹ ወይም ደግሞ አውሬ እንዳይበላቸው፥ ሌባም እንዳይወስዳቸው እረኞቹ ተራ ገብተው ያግዷቸዋል፡፡ ወደ ለመለመ መስክ ወስደው ሳር ቅጠል ያስግጧቸዋል፡፡ ጊዜ ድራሽ ሲሆን ደግሞ ወደ ወንዝ አውርደው ውሃ ያጠጧቸዋል፡፡ ከብት ጠባቂዎቹ ይህንን ዕለታዊ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ተባብረውና ተራ ገብተው ነው፡፡ ተራቸው እንዳይፋለስባቸውም ሁሉም በኅብረት ይጠበቁታል፡፡ የእያንዳንዱ እረኛ ተራ እንዳይፋለስ ሁሉም ተባብሮ በተስማማበት ውል መሠረት የየድርሻውን ይወጣል፡፡

ይህ የእረኞቹ ሥነስርዓት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ባኅልና ልምድ ይዞ የሚቀጥል ነው፡፡ የዚህን ስምምነት ተራ አንዱ ዋልጌ ከብት ጠባቂ ካፋለሰ፥ ነገር ተበላሸ ማለት ነው፡፡ መፎካከር ይመጣል መዘባራት ይሰፍናል፡፡ ያንተ ተራ ነው ያንተ ተራ ነው መባባል ይከተላል፡፡ በዚህ መካከል ከብቶቹን የሚያያቸው፥ የሚፈቅዳቸው፥ የሚመልሳቸው፥ ይጠፋል፡፡ አንዱ ሰነፍ እረኛ ባስከተለው የተራ ማፋለስ ምክንያት፥ የዕረኞቹ ኅብረት ይናጋል፡፡ የዕረኞች መዘባራት ደግሞ፥ የከብቶችን መጥፋት ያስከትላል፡፡ ይህም በበኩሉ ዋይታና ለቅሶን ያመጣል፡፡ "በማር ጠብታ ሀገር ተፈታ" ፥ በዋልጌ እረኛ ከብቶች ለቀማኛ ቢሉት ኋላ አይጠቅምም

ይህንን በከብት ጠባቂዎች የሚከሰተውን ሁኔታ እንደ ምሳሌ ጠቀስን እንጅ፤ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ኑሮና ሰባዓዊ ሕይወት፥ በልዩ ልዩ ተቋማትና ስብስቦች፥ እንዲሁም የፖሊቲካ ድርጅቶች ጎልቶ የሚታይ ሀቅ ነው፡፡ አብሶማ በተቃዋሚው ጎራ ያለው መፎካከርና መዘባራት ይህ ነው አይባልም ቢባል ማጋነን ነው ሊባል አይቻልም፡፡ ለአንድ ዓላማና ግብ ተስማምተው፥ ምለው ተገዝተው፥ በአደባባይ ተፈራርመው፥ በጉባዔ ተፈጣጥመው፥ የተፈራረሙበት ቀለም ሳይደርቅ፥ የተዋዋሉበት ውል ሂደቱ ሳያልቅ፥ አንዱ ወይም ሌላው ሞገደኛ በማፈንገጡ ብቻ፥ ብዙ የተለፋበት፥ ሕዝቡ ትልቅ ተስፋ ያደረገበት፥ በአንፃሩ ደግሞ ፀረ ኅብረት የሆነው ክፍል የተርበተበት ጥረት ሁሉ መና ሆኖ ይቀራል፡፡ ቀርቷልም፡፡ ይህም የኅብረቱ ሰነድ በተፈረመ ማግስት በሚገባ ታይቷል፡፡ አንተ ትብስ እኔ ልብስ በመባባል ኅብረቱን አጥንክሮ ብሔራዊ ግዳጅን መወጣቱ ቀርቶ፥ አንተ ነህ እርሱ ነው በመባባል የእርስ በእርስ

መወቃቀስ፥ መወነጃጀል፥ ጣት ይቀሰራል፡፡ ዋናው ብሔራዊ ዓላማና አጀንዳ ይጠፋል፡፡ ጠላት ጮቤ ይረግጣል፡፡ በወያኔ ጎራ ኀይላ ይዘፈናል፡፡ መለስና ተባባሪዎቹ ላሜ ወለደች ይላሉ እያሉም ናቸው፡፡ እርስ በእርስ የሚወነጃጀሉትን ጠላቶቹን እያየ ይስቃል፡፡ ያፌዛል፥ ይንቀል፡፡ እሳትና ገለባ ያድርጋችሁ ይላቸዋል፡፡ ተቃጥለው እንዲከስሙ ቤንዚን ያርከፈክፍባቸዋል፡፡ አመዳቸውን እየበተነ በንፋስ ይጫወታል፡፡ በአሁኑ ወቅት እየተከሰተ ያለው ይህ ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህ ግን እንዲህ ሆኖ አይቀርም፡፡ ሁሉም በሰፈረው ቁና ይሰፈርበታል፡፡ የጁን ያገኛል፡፡ በመጨረሻም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሚዛናዊ ፍርድ ማግኘቱ የማይቀር ነው፡፡

ሀቀኛ ታጋዮች ግን “ ውርድ ከራሳችን ብለው” የኢትዮጵያን ሕዝብ አክብረው፥ የገቡበትን ቃል ኪዳን ጠብቀው፥ ብኩርናቸውን ለጭብጥ ምስር ሳይሸጡ፥ መርኃ-ግብራቸውን ለሥልጣን ፍርፋሪ ሳይለውጡ፥ ለሚደርስባቸው መሠዋዕት ሳይረበሹ፥ ከትግሉ ፍልሚያ ሳይሸሹ፥ ዕምነታቸውን ሳይሸረሽሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ሳይደራደሩ፥ ለማይቀረው ሕዝባዊ ድል ይታገላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስኪጎናፀፍ ድረስ !

ያ እስኪመጣ ድርስ እናም ደግሞ፥ ቆርጠኛና ሀቀኛ የትግል ምዕራፍ አስተማማኝ ደረጃ እስኪይዝ፥ የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል፡፡ ያልተዘጋ ቤት ደግሞ የሌባ መጫዎቻ ይሆናል፡፡ ብሔራዊ ምሥጢር ይዝረከረካል፥ ይባክናል፡፡ ለጠላት መጠቀሚያ ይሆናል፡፡ “ቤታቸውን ሳይዘጉ እየቀሩ በሌባን ያማርራሉ” ተብለው ይፌዝባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደም እንባ ያለቅሳል፡፡ “ ይህ የተረገመ ትውልድ መች ይተባበራል” ተብሎ ትውልዱ ይወቀሳል፡፡ የተያዘ- የተረዘዘው ሁሉ በዚህ አሳረኛ ትውለድ ያማርራል፥ ያመካኛል፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ መላ ቅጡ ይጠፋበታል፡፡ መልካም መካሪ ሽማግሌ አንገት ይደፋል፡፡ አንጋፋ አዛውንት ያዝናሉ፡፡ ምሁሩ ድፍረት ያጣል፡፡ ብሔራዊ ራዕይ ማየት ይሳነዋል፡፡ ጀግና ይሰወራል፡፡ ዜጋ ሁሉ ሰማይ ምድሩ ይደፋበታል፡፡ መላ ቅጡ ይጠፋበታል፡፡ “ኢትዮጵያ የምድር ሲዖል ነች“ ሲባል የነበረው የጠላቶቿ ሀኬት ወደ ዕውነት ተለውጦ ያየዋል፡፡ ያገኘዋል፡፡ የተያዘ የተረዘዘው ኢትዮጵያዊ ሀሞቱ ይፈስስበታል፡፡ ሁሉም ሀገሩን ለቅቆ መውጣት ይፈልጋል፡፡ ይወጣል፡፡ የሄዳል፡፡ ይበርራል፡፡ እንደ ዘጽዓት ይሰደዳል፡፡ ፥ “ከእንግዲህ፥ ወያኔ እስካለ፥ ሀገሬን አያሳየኝ” ብሎ ይምላል፥ ይገዘታል፡፡ ሀገርን ለጠላት አሳልፎ ማስረከብ የዕለት ተዕለት ተግባር ይሆናል፡፡ “ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል” እንዲሉ፥ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በቀደደው ሀገርን አሳልፎ ሰጥቶ የመፈርጠጥ አሳፋሪ ጎዳና፥ ሁሉም ሀገሩን ለቅቆ መሄድን የመርጣል፡፡ ሀገር ባድማ ትሆናለች፡፡ ባድማ ጠባቂ በመጥፋቱም፥ ሀገር፥ የሀገር አጥፊዎች መጫዎቻ ትሆናለች፡፡ የተቃዋሚው ጎራ እርስ በእርስ መራኮትና መዘባራት ያስከተለው ብሔራዊ ጥፋት መሆኑን ግን ስንቶቻችን እንደምንገነዘበው በዕርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ያንንማ ሁሉም ተግንዝቦት ቢሆን ኖሮ፥ የሀገራችን የፖለቲካ መልከአ-ምድር ሌላ ገፅታ በኖረው ነበር፡፡

የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ማደሩ ብቻ ሳይሆን፥ ባለቤት የሌለው፥ ዎናም ነው:: ዎና ቤት ደግሞ የተባይና የአውሬ መፈንደቂያ ይሆናል:: ማንም የሚጫዎትበት፥ አላፊ አግዳሚ የሚቀልድበት፤ ባዕዳን እንደልባቸው የሚደነክሩበት፥ የሚፈነጩበት ይሆናል:: ሀገርን ዎና አድርጎ፥ ለበላዒ-ሰብ አስረክቦ፥ ሕዝብን አሰድዶ፥ "ሀገር ጠፋ፥ ባኅል ተሻረ፥ ኃይማኖተ ረከሰ፥ ድንበር ተደፈረ፥ ሰብዓዊ መብት ተረገጠ፥ የኤድስ ቫይረስ ሕዝብ ጨረሰ፥ ሥራ-ፈት በዛ፥ የነዳያን ብዛት ሀገሪቷን አጥለቀለቃት፥" ወዘተ እያሉ ደረት ቢደልቁ፥ ምሾ ቢደረድሩ፥ ቢያርሩ ቢተክኑ፥ መፍተሄ አይመጣም:: በሀገሪቱ መሠረታዊ የችግር ምክንያቶችና መንስዔዎች ትኩረትን በመስጠት፥ ርብርቦሽ ሳያደርጉ፥ ብሎም እነርሱ የሚወገዱበትን መፍተሄ ሳይፈልጉ፥ የችግሮቹ ምክንያቶች በአስከተሉት ውጤት ላይ ብቻ ቢያዝኑ ቢተክኑ፥ ከንቱ ድካም እንጅ መፍተሄ አይገኝም:: ይህን ሃቅ ደግሞ ለአለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት ኖረንበት፥አይተነዋል:: ሀገሪቱ የፍክክር ቤት በመሆኗ፥ አብዛኛውም ለጎጡ፥ ለክልሉና ለብሔሩ ብቻ ቅድሚያና ትኩረት እየሰጠ ፥ ለብሔራዊ ጥቅም፥ ለሀገራዊ ነፃነት፥ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚያስበው ቁጥር እያነሰ መሄዱን ያልተገነዘበ ዜጋ የለም ለማለት ያስቸግራል:: ዜጎች በብሔራዊ ደረጃ ፥ ለሀገር አቀፍ ጥቅምና ለማላው ሕዝብ ነፃነትና መብት ማሰብን እየተው በሄዱ ቁጥር፥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ቀስ በቀስ እየጠፋች የሚትሄድ መሆኗን መገመት አስቸጋሪ አይመስለንም:: የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ ለግል ድርጅቶቻቸው ጥቅምና ለግለሰቦች ውዳሴ ከንቱ ብቻ ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ፥ ሌላውም እንደዚሁ ለየግል ብሔሩና ጥቅሙ የሚሯሯጥ ከሆነ፥ በዋልጌው እረኛ ምክንያት እንደጠፉት ከብቶች፥ ኢትዮጵያም ከነሕዝቧ የምትጠፋበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብሎ ስጋትን መግለጽ፥ እንደ ቦታ ሰዳች ሊያሸብር፥ ሊያስደነግጥ የሚችል ጮኸት ሊሆን አይገባውም:: በተለይ የወያኔን ማንነት ከጥንቱ-ከጧቱ ደኅና አድረግው ከሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች፥ ድርጅቶች የሚደወለውን የማስጠንቀቂያ ደወል መስማት ፥ ኢትዮጵያን ማዳን አለብን ለሚለው ክፍል ሌላ አማራጭ አይኖረውም:: የወያኔን ማንነት፥ የኢትዮጵያን ስትራተጅያዊ ጠላት ምንነት በሚገባ መረዳት፥ ለሀገራችን ችግር መፍተሄ ፍለጋ ጥረት፥ የመጀመሪያው ዕርምጃ ነው ተብሎ ይታመናል::

ዛሬ በአንዳንድ አካባቢ የሚታየው መፍጨርጨር፥ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ነፃነትና ኅልውና፤ ብሎም የዜጎቿን አንድነት ማስከበር ሳይሆን፥ የተሸመደመደ ጥገናዊ ልውጥ በማምጣት የሕዝቡን ሀገራዊ ትግል ለማኮላሸት የሚደረግ ብኩን ጥረት ነው:: ይህም አመለካከት የወያኔን ዕድሜ ቀጣይ የሆነ ክስተት ከመሆን አያልፍም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የወያኔን ዕድሜ ለመቀጠል በሚደረገው አመለካከትና ሂደት፥ ታከፋይ መሆንን ጭራሽ የሚፈልግ አይደለም:: ታዲያ የሀገራችን ጉዳይ የፉክክር ቤት ሆኗል ለማለት የሚያስችለውም፥ ይህ ሀቅ ይመስለናል:: ሁሉም ተባብሮ ሀገሪቱን ከገባችበት አዘቅት ማዳን ሲቻል፥ በእልህና በፉክክር፥ ነገር-ዓለሙን መተውና ብሎም፥ ፥ጊዜ ሰጥቶታልና፥ ወያኔ ያሻውን ያድርግ" ከሚል አሳፋሪና በታሪክም አስጠያቂ በሆነ የጥላቻና የቂም በቀል አዙሪት መግባት፥ በዘለቄታ መልኩ ኢትዮጵያን የሚጎዳ መሆኑ

መታወቅ ይኖርበታል። በዕልህና በጥላቻ ደግሞ፥ ሀገር ቀርቶ የግል ጓደኝነት ውጤት አይኖረውም። በታሪክና በትውልድ ፊት ሁሉም፥ ማንኛውም፥ በግልም ይሁን በጋራ ተጠያቂ እንደሚሆን ማወቅ ያስፈልጋል። ከኅልፈተ-ወያኔ በኋላ፥ ከሕዝብ ብያኔ ለማምለጥ በሚደረገው መርበትበት፥ እነ-እገሌ አሳስተውኝ ነው፥ ይህ እነ ርሱን እንጅ እኔን አይመለከተኝም። ታዝዤ ነው፥ ሰው አሳስቶኝ ነው..... ወዘተ የሚል ዝባዝንኬ፥ ሀገር በማጥፋት ወንጀል ከማስጠየቅ የሚያድን አይሆንም።

ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ከተሰጡት የተፈጥሮ ፀጋዎች መካከል አንዱ፥ አዕምሮውን በመጠቀም ከፉውንና ደጉን መለየት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ጤናማ አዕምሮ ያለው ሰው ምን ጊዜም ቢሆን፥ ሆን ብሎ፥ የሀገሩን ጥፋት ይመኛል ብሎ ለማመን ቢያስቸግርም፥ ዛሬ በሀገራችን የሚፈፀመው ግን ይህ ነው። ነፃ እናወጣዋለን ብለው የታገሉለትን ዓላማ እያሳኩ፥ ሌላውን የሀገሪቱ ክፍል ወያኔዎቹ ቢበድሉና ቢጎዱ፥ ምናልባት ላያስደንቅ ይችል ይሆናል። ሀገሬን ከወያኔ መንጋጋ አላቅቃለሁ የሚለው ክፍል ፥ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው፥ ሕዝብንና ሀገርን የሚጎዳ ተግባር ሲፈጽም ማየት ግን ለሰሚው ግራ ይሆናል።

የተቃዋሚው ጎራ በአንድ አለመቆም ፥ የቱን ያህል ሀገርና ሕዝብ የሚበድል መሆኑን ለማንም የተሰወረ አይደለም ብለን ማመን እንፈልጋለን። ታዲያ፥ ጉዳዩን የማመንና ያለማመን ሳይሆን፥ ሁሉም እያንዳንዱ፥ በጋራም ይሁን በግል ኃላፊነት መኖርንና ተጠያቂ መሆኑን በግዴለሽነት እያየ ስለሚያልፈው ብቻ ነው የሚለውን ድምዳሜ ለመውሰድ እንገደዳለን። የጋራን ቤት በፉክክር ብቻ ሳይዘጉ መቅረት፥ ለጠላት አሳልፎ እንደመስጥት ይቆጠራል ። የጋራን ሀገራዊ ችግር በጋራ መፍታት ካልተቻለ፥ ኃለፊነቱንና ተጠያቂነቱን በጋራና በግል መሸከምና መቀበል ሊኖር ነው። እያንዳንዱ የድርጅት መሪም ይሁን አባል፥ ለሰራው ብቻ ሳይሆን፥ መስራት የሚጋባውን ሳይፈጽም በመቅረቱም ጭምር፥ በታሪክም በሕዝብ በመጭው ትውልድም ፊት የማይጠየቅበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ይህ እንግዲህ የያንዳንዱን የህሊና ወቀሳና ፍርድ ሳይጨምር ማለት ነው። ለነገሩማ፥ አንድ ሰው ተጠያቂ መሆን ያለበት፥ ከማንም በላይ በመጀመሪያ ለራሱ ኅሊና መሆን አለበት ብለን እናምናለን። ይኸን የምንለው፥ የኅሊናችን ተገዥዎች በመሆናችን እንጅ ሌላ ዓብነት ኖሮን አይደለም። ለራሱ ኅሊና ተገዥ ሳይሆኑ፥ ለድርጅትም ይሁን ለሀገር የሚበቃ ኃላፊነት መሸከም የሚቻል አይመስለንም። የፉክክር ቤትም ሳይዘጋ የሚያድረው፥ ሁሉም እያንዳንዱ የየድርሻውን ሲወጣ ሳይችል ሲቀር መሆኑ ምንም የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም። ይህን ሀቅ መገንዘብ ካለተቻለ፥ ቤቱም ክፍት ይሆናል። ክፍት ቤት ደግሞ፥ ማንኛውም ጠላት ዘው ብሎ እየገባ ያሻውን ከማድረግ የሚያግደው ኃይል የለም። በወያኔ አገዛዝ የወደቀችው ሀገራችንም ሁኔታ ለዚህ መልካም ማስረጃ ነው።

"ክፍት ይዋል ክፍት ይደር ብለው ሲመርቁ፥
ቤቱም ክፍቱን ቀረ ጀግኖቹም አለቁ"

እየተባልን በታሪክና በትውልድ ፊት እንዳንፈረድ፥ እንዳንወገዝ፥ተባብርን፥ ኀብረታችንን አጠንክረን በመታገል፥ ሀገራችንን ከጥፋት ከማዳን ሌላ አማራጭ አይኖረንም፡፡ ሀገርን ማዳን የሚቻለው ደግሞ፥ የመላውን ሕዝብ ኃይልና ጉልበት አስተባብሮ ለብሔራዊ የነፃነት ትግል ሲያሰልፉት ብቻ ነው፡፡ ለምን ቢባል፥ የሕዝብን አመፅ የሚበግረው ኃይል ስለማይኖር ነው፡፡